# የአፈር ማዳበሪያ ፍላጎት፣ ግዥ እና ሥርጭት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 977/2016 ዓ.ም

ጥቅምት 2016 ዓ.ም

የገንዘብ ሚኒስቴር

<u>አዲስ አበባ</u>

# የአፈር ማዳበሪያ ፍላጎት፣ ግዥ እና ሥርጭት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 977/2016 ዓ.ም

በሥራ ላይ ባለው መመሪያ መሠረት የሚፈፀመው የአፈር ማዳበሪያ ግዥ የሚወስደው ጊዜ ረጅም በመሆኑ ሀገራችን በዓለም ገበያ በሚኖረው የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ውድድር ላይ ተጠቃሚ እንዳትሆን እና የአፈር ማዳበሪያ ለአርሶና ከፊል አርብቶ አደሩ በሚፈለገው ጊዜ ማቅረብ እንዳይቻል ያደረገ ስለሆነ መመሪያውን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአፈር ማዳበሪያን በወቅቱ፣ በሚፈለገው የጥራት መስፈርት፣ ዓይነት፣ መጠን፣ ቦታ እና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ በዘርፉ ምርትና ምርታማነት እንዲጎለብት በማድረግ አርሶና ከፊል አርብቶ አደሩን በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ የሚያደርግ ቀልጣፋና ውጤታማ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአፈር ማዳበሪያ ፍላጎት፣ ግዥ እና ስርጭት አፈፃፀምን ለመምራት የወጣ መመሪያ ቁጥር 977/2016 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) "አስመጪ" ማለት በግብርና ባለሥልጣን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው የአፈር ማዳበሪያን ከውጭ አምራች ወይም አቅራቢ ገዝቶ በሀገር ውስጥ ለማከፋፈል የተመረጡ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ በሚኒስቴሩ የሚመረጡ የሀገር ውስጥ የግል ድርጅቶችን ያጠቃልላል፡፡
2) "ቴክኒካል ኮሚቴ" ማለት በዚህ መመሪያ አንቀፅ 11 የተጠቀሰውን ተግባር እና ኃላፊነት እንዲያከናውን በዚህ መመሪያ የተቋቋመ ኮሚቴ ነው፡፡
3) "ቦርድ" ማለት በዚህ መመሪያ በተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች የሚፈፀመውን የማዳበሪያ ግዥ ውጤት መርምሮ የሚያፀድቅ የአስመጪው ድርጅት ቦርድ ነው፡፡

4) "የአፈር ማዳበሪያ" ማለት በማዳበሪያ ማምረትና ንግድ ድርጅት አዋጅ ቁጥር 137/1991 አንቀጽ 2(1) የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

5) በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀው ለሴትም ያገለግላል፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የአፈር ማዳበሪያ ፍላጎት፣ ግዥ እና ሥርጭት ሥራ ላይ በሚሳተፉ አካላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ የአፈር ማዳበሪያን ለአርሶና ከፊል አርብቶ አደሩ በሚፈለገው ጥራት፣ ዓይነት፣ መጠን፣ በተመጣጣኝ ዋጋ እና በወቅቱ ለማቅረብ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## በአፈር ማዳበሪያ ፍላጎት፣ ግዥ እና ሥርጭት ሂደት የሚሳተፉ የአስፈፃሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

## 5. የክልል መንግሥታት

የክልሉ መንግሥት፡-

1) የክልሉን ዓመታዊ የአፈር ማዳበሪያ ፍላጎት በዓይነት እና በመጠን እንዲሁም ለግዥው የሚያስፈልገውን የብድር ፍላጎት በመለየት ግብርና ሚኒስቴር በሚወስነው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ያሳውቃል፤ ለተፈቀደ በጀት ዋስትና ይወስዳል፤ ቀልጣፋ እና የዘመነ የግብይት ሥርዓቶች ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤ ብድር አመላለሱንና አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

2) የአፈር ማዳበሪያ ፍላጎት የአርሶና ከፊል አርብቶ አደሩን ማማከሩን፣ የእርሻ መሬትን ስፋት፣ የአፈር ጥናትን እና የምርምር ውጤቶችን መሠረት በማድረግ ለመስኖ፣ ለበልግ እና ለመኸር ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለውን በየክልሉ ግብርና ቢሮዎች ታሳቢ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

3) ከብሔራዊ ባንክ ለሚፈቀድ የግብዓት መግዣ ብድር ለባንክ የብድር ጥያቄ ያቀርባል፤ በብድር እንዲቀርብ በተደለደለው የአፈር ማዳበሪያ መጠን ለሚከፈለው ገንዘብ ከአስመጪው ድርጅት እና ከብድር አቅራቢው ባንክ ጋር የሦስትዮሽ እና አምስትዮሽ ውል ይፈራረማል፤

4) ከግብርና ሚኒስቴር በሚደርሰው የመርከብ ድልድል መሰረት የአፈር ማዳበሪያ በየመዳረሻ ጣቢያ በክልሉ ግብርና ቢሮዎች ወይንም በክልሉ ህብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች በአግባቡ መደልደሉንና ተረካቢ ዩኒየኖች መረካበቸውን ያረጋግጣል፤

5) ከግብርና ሚኒስቴር በሚደርስ የማስረከቢያ ዋጋ ላይ ተመስርቶ የመሸጫ ዋጋ ይወስናል፤

6) ከአስመጪው ድርጅት በሚደርሰው የክፍያ ጥያቄ መሠረት ተገቢውን ክፍያ በወቅቱ እንዲፈፅምና የሂሳብ ማስታረቅ ስራዎችን መከናወኑን ያረጋግጣል፤

7) ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ ከተግባርና ኃላፊነቱ የሚመነጩ ማናቸውንም ተግባራት ያከናውናል፡፡

6. <u>የግብርና ሚኒስቴር</u>

1) ከክልሎች የአፈር ማዳበሪያ ፍላጎት የሚቀርብበትን የጊዜ ሰሌዳና ሂደት በተመለከተ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ እንደአስፈላጊነቱ ወቅታዊ ማሻሻያ ያደርጋል፤

2) ከዚህ በላይ ከክልሎች የቀረበለትን ፍላጎት በመለየት፣ በማደራጀትና በመተንተን ለምርት ዘመኑ የሚያስፈልገውን የአፈር ማዳበሪያ መጠን በመለየት እንደአስፈላጊነቱ የ3 ዓመት ተንከባላይ የፍላጎት ዕቅድ በዲጂታል ዘዴ ያዘጋጃል፤

3) ከክልሎች በዓይነት እና በመጠን የሚቀርብለትን የአፈር ማዳበሪያ ፍላጎት በመተንተን ከውጭ መገዛት ያለበትን ዓመታዊ የአፈር ማዳበሪያ መጠን ይወስናል፤

4) በተዘጋጀው ዕቅድ መሠረት ከውጭ ተገዝቶ ለሚገባው የአፈር ማዳበሪያ የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ ፍላጎት ግምትና የጊዜ ሰሌዳ አዘጋጅቶ

ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያሳውቃል፤ በባንኩ የተፈቀደውን የገንዘብ መጠን በግብዓት ዓይነት ለይቶ ክልሎች እንዲያውቁት ያደርጋል፤

5) ዝርዝር መግለጫ በማዘገጀት ዓመታዊ የአፈር ማደበሪያ ግዥን እና ወደ አገር ውስጥ የሚገባበትን የጊዜ ሰሌዳ በተመለከተ የአፈር ማዳበሪያ በየክልሉ የመርከብ ድልድል እና የመረከቢያ ጣቢያዎች በዓይነት እና መጠን በመለየት አስመጪዎች እንዲያውቁት ያደርጋል፤

6) በክልሎች፣በአስመጪው ድርጅት እና የመተማመኛ ሰነድ (L/C) በሰጠው ባንክ መካከል የክፍያ ማስታረቅ ሥራ ጊዜውን ጠብቆ የተከናወነ መሆኑን ይከታተላል፣ያረጋግጣል፤

7) ለአፈር ማዳበሪያ አስመጪዎች የግብርና ባለሥልጣን በሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መሠረት የአስመጪዎችን አፈፃፀም እየገመገመ ከውጭ የሚያስመጡትን የአፈር የማዳበሪያ ድርሻ መጠን ይወስናል፤

8) ከአስመጪዎች የቀረበ የአፈር ማዳበሪያ የዋጋ ግንባታ ላይ ተመስርቶ የማስረከቢያ ዋጋ ይወስናል፤ ነባራዊ ሁኔታዎችን በማገናዘብ ድጎማ እንዲደረግ ለመንግሥት ያቀርባል፤

9) ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ ከተግባርና ኃላፊነቱ የሚመነጩ ማናቸውንም ተግባራት ያከናውናል፡፡

7. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር</u>

1) ለግብርና ግብዓት መግዣ የሚውል ገንዘብ ይፈቅዳል፤ ከክልሎች የሚቀርብለትን የብድር ጥያቄ ያፀድቃል፤ ብድሩን በወቅቱ ተመላሽ እንዲሆን ያደርጋል፤
2) L/C ለሚከፍት ባንክ የበጀት ዋስትና ይሰጣል፤ በወቅቱ በጀቱን እንዲለቀቅ ያደርጋል፤
3) የአፈር ማዳበሪያን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ለሚያስፈልጉ ወጪዎች ዋስትና ይሳጣል፤
4) መንግሥት ለመንግሥት ግዥ (G2G) በብድር ለሚገዛ የአፈር ማዳበሪያ ዋስትና ይሰጣል፤
5) ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ ከተግባርና ኃላፊነቱ የሚመነጩ ማናቸውንም ተግባራት ያከናውናል፡፡

8. <u>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ</u>

1) ከግብርና ሚኒስቴር በሚቀርብለት የውጭ ምንዛሪ ፍላጎት ግምትና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ለምርት ዘመኑ የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ በመመደብ ለግብርና ሚኒስቴር ያሳውቃል፤

2) ለምርት ዘመኑ ባንኩ የመደበውን የውጭ ምንዛሪ እና ገንዘብ የግብርና ሚኒስቴር አስተካክሎ በሚያቀርበው የጊዜ ሠሌዳ መሰረት ለአፈር ማዳበሪያ አስመጪ ድርጅቶች የመተማመኛ ሰነድ (L/C) ለሚሰጠው ባንክ ያስተላልፋል፤

3) በተገባው በአፈር ማዳበሪያ ግዥ ኮንትራት ውል መሰረት የሚያስፈለገውን የውጭ ምንዛሪ እና ገንዘብ ይፈቅዳል፤

9. <u>ባንክ</u>

1) ለምርት ዘመኑ ለሚገዛ የአፈር ማዳበሪያ በአስመጪ ድርጅቶች በሚገባ የግዥ ኮንትራት ውል መሰረት ለአስመጪ ድርጅቶች የመተማመኛ ሰነድ (L/C) ይከፍታል፤

2) ከክልል መስተዳደሮች በሚቀርቡ የብድር ጥያቄ መሰረት የሶስትዮሽ እና አምስትዮሽ ውል ይገባል፤ ክፍያዎችን ይፈፅማል፤

3) ጥቅም ላይ ያዋለ የብድር መጠን እና ዕዳ ለተባደሪዎች ያሳውቃል፤ ከተባዳሪ አካላት ጋር በመሆን የሂሳብ ማስታራቅ ስራዎች ያከናውናል፤

4) አስመጪ ድርጅቱ የመተመመኛ ሰነድ (L/C) እንዲከፈትለት ጥያቄ ባቀረበ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡

10. <u>የቦርዱ ተግባርና ኃላፊነት</u>

ቦርዱ፡-

1) በዚህ መመሪያ መሠረት የሚፈፀመው የአፈር ማዳበሪያ ግዥ መሰረታዊ የግዥ ሕግ መርሆችን ተከትሎ የተከናወነ/የተፈፀመ መሆኑን ያረጋግጣል፤

2) ለመንግሥት የሚያስገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከግምት በማስገባት የአፈር ማዳበሪያ በዚህ መመሪያ የተፈቀደውን አግባብነት ያለውን የግዥ ዘዴ ተከትሎ እንዲገዛ ይወስናል፤

3) በቴክኒካል ኮሚቴው ተገምግመው የቀረቡ የጨረታ ወይም የግዥ ግምገማ ሪፖርቶችን መርምሮ ያፀድቃል፤
4) በዚህ መመሪያ መሰረት የሚፈፀመውን የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

## 11. የቴክኒካል ኮሚቴ አደረጃጀት

የቴክኒካል ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

ሀ) ከግብርና ሚኒስቴር የኮሚቴው ሰብሳቢ

ለ) ከገንዘብ ሚኒስቴር አንድ አባል፤

ሐ) ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አንድ አባል፤

መ) ከመንግሥት ግዥ አገልግሎት አንድ አባል፤

ሠ) ከአስመጪው ድርጅት አንድ አባል፤

## 12. የቴክኒካል ኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

1) በአስመጪው ድርጅት ተዘጋጅቶ የቀረበውን የጨረታ ውጤት ከዓለም የገበያ ዋጋ፣ ከፋይናንስ አቅርቦት፣ ከክፍያ ጊዜ ከመሳሰሉት አኳያ በመገምገም ከራሱ የውሳኔ ሀሳብ ጋር ለቦርዱ አቅርቦ ያፀድቃል፡፡
2) ሌሎች አስፈላጊ ተያያዝ ጉዳዮችን በተመለከተ ቦርዱን ያማክራል፡፡

## 13. የአፈር ማዳበሪያ አስመጪ ተግባርና ኃላፊነት

በሚሰጠው ድርሻ መሰረት የአፈር ማዳበሪያን ከውጭ ለማስመጣት በግብርና ባለሥልጣን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ድርጅት፡-

1) በግብርና ሚኒስቴር የተዘጋጀውን አጠቃላይ የምርት ዘመኑን የአፈር ማዳበሪያ ግዥ መጠንና ዓይነት፣ የጊዜ ሰሌዳ፣ ዝርዝር መግለጫ (specification) መረጃ ተከትሎ የራሱን የአፈር ማዳበሪያ ማስመጣት ዕቅድና ዝግጅት ያደርጋል፤

2) ከአበዳሪው ባንክ ለማዳበሪያ ግዥ የሚውል የተፈቀደውን ብድር በፀደቀው ጊዜ ሠሌዳ መሰረት የመተመመኛ ሰነድ (L/C) እንዲከፈት ጥያቄ ያቀርባል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

3) ለራሱ ለሚያስመጣውን የአፈር ማዳበሪያ የሚያስፈልገውን ብድር በቅድሚያ ያስፈቅዳል፤

4) አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ጨረታ ሰነድ ያዘጋጃል፤

5) የዓለም የማዳበሪያ ዋጋ ሁኔታን በቅርበት በመከታተል የአፈር ማዳበሪያ ዋጋ በአንፃራዊነት በሚቀንስበት ወቅት የጨረታ ተሳትፎ ማስታወቂያ ጥሪ አዘጋጅቶ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ እንዲወጣ ያደርጋል፤

6) ለአፈር ማዳበሪያ ግዥ ተቀባይነት ያላቸውን የቴክኒካልና የዋጋ መመዘኛ መስፈርቶችን በመጠቀም ተጫራቾችን ያወዳድራል፤ አሸናፊ ይለያል፤ ውጤቱን በቴክኒክ ኮሚቴው አማካኝነት ለቦርድ አቅርቦ ያፀድቃል፤

7) በዚህ መመሪያ በተፈቀደው የግዥ ዘዴ መሠረት ከሚመረጠው የአፈር ማዳበሪያ አቅራቢ ጋር የአቅርቦት ውል ተዋውሎ የመተማመኛ ሰነድ (L/C) ይከፍታል፤

8) በግብርና ሚኒስቴር በሚወስነው የማስረከቢያ ዋጋ ተመን መሠረት ለአርሶና ከፊል አርብቶ አደሩ የሚያቀርበውን የአፈር ማዳበሪያ በተመጣጣኝ ዋጋ ያቀርባል፤

9) ከክልሎች እና የመተማመኛ ሰነድ (L/C) ከሰጠው ባንክ ጋር በመተባበር የክፍያ ማስታረቅ ሥራ ጊዜውን ጠብቆ ያከናውናል፤

10) ከተግባርና ኃላፊነቱ የሚመነጩ ሌሎች አስፈላጊ ተያያዝ ጉዳዮችን ያከናውናል፡ ፡

## ክፍል ሦስት

## የአፈር ማዳበሪያ ግዥ አሠራር

### 14. የግዥ ዘዴ

የአፈር ማዳበሪያ ግዥ የሚከተሉትን ዘዴዎች በመከተል ሊፈፀም ይችላል፡፡

#### 14.1 ግልጽ ጨረታ

የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ለማንኛውም የውጭ አቅራቢ ግልፅና እኩል የመወዳደር ዕድል በሚሰጥ ግልጽ ጨረታ ሊከናወን ይችላል፡፡

#### 14.2 ውስን ጨረታ

ከዚህ በላይ በአንቀፅ 13.1 እና በግዥ አፈፃፀም መመሪያው አንቀፅ 23 የተደነገገው ቢኖርም የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ጅኦግራፊያዊ የአምራች ድርጅቶችን መገኛ፣ ከባህር በር ያላቸውን ቅርበት፣ ከንግድ ሥርዓት አግባብነት አኳያ ታይቶ በውስን ጨረታ ከሦስት ላላነሱ አምራቾች ወይም አቅራቢዎች በሚላክ ግብዣ መሰረት የሚቀርቡ ተጫራቾችን በማወዳደር ከጨረታው አሸናፊ አምራች ወይም አቅራቢ ድርጀት ጋር የዋጋ ማስተካከያ በሚደረግበት የማዕቀፍ ውል መሠረት እንዲገዛ በቦርዱ ሊወሰን ይችላል፡፡

#### 14.3 ቀጥታ ግዥ

ከዚህ በላይ በአንቀፅ 13.1 እና በግዥ አፈፃፀም መመሪያው አንቀፅ 23 የተደነገገው ቢኖርም የአፈር ማዳበሪያ አቅራቢው አንድ ብቻ ሲሆን ወይም በቂ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ መኖሩ በቦርዱ ሲረጋገጥ የአፈር ማዳበሪያ ከአንድ አምራች ወይም አቅራቢ ድርጅት ጋር የዋጋ ማስተካከያ በሚደረግበት የማዕቀፍ ውል መሠረት እንዲገዛ በቦርዱ ሊወሰን ይችላል፡፡

14.4 <u>መንግሥት ለመንግሥት የሚደረግ የአፈር ማዳበሪያ ግዥ (G2G)</u>

ከዚህ በላይ በአንቀፅ 13.1 የተደነገገው ቢኖርም የማዳበሪያ ግዥ ከሀገራችን ጋር ያለውን ሁለትዮሽ ግንኙነት መሰረት በማድረግ የዓለም ገበያ ዋጋን መሠረት ያደረገ የዋጋ ማስተካከያ በሚደረግበት የማዕቀፍ ውል መሠረት ወይም የፕሪሚየም ዋጋ ማስተካከያ (Procurement on Premium Price Base) አሠራርን ተከትሎ እንዲገዛ በቦርዱ ሊወሰን ይችላል፡፡

15. <u>የጨረታ ሥነ-ሥርዓት</u>

1) በግዥ አፈፃፀም መመሪያው የተደነገገው ቢኖርም የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ጨረታ አየር ላይ የሚቆየው ከ10 እስከ 15 ቀን ላልበለጠ ጊዜ ነው፡፡
2) ተጫራቹ ለጨረታ ማስከበሪያ የሚያሲዘው መጠን ከ0.5% እስከ 6% ይሆናል፡፡
3) በግዥ አፈፃፀም መመሪያው የተደነገገው ቢኖርም በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) በአሸናፊነት የሚመረጠው አቅራቢ በውሉ መሠረት ባለመፈፀሙ ለሚደርሰው ጉዳት ማካካሻ የሚያሲዘው የውል ማስከበሪያ እስከ 5% እንዲሆን በቦርዱ ሊወሰን ይችላል፡፡

# ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

16. **ስለሌሎች ተሳታፊዎች**

በሚሰጣቸው ድርሻ መሰረት የራሳቸውን የውጭ ምንዛሪ ምንጭ ተጠቅመው የአፈር ማዳበሪያን ከውጭ በማስመጣት ማከፋፈል የሚችሉ አስመጪዎች በልዩ ሁኔታ ተሳታፊ የሚሆኑበት አሠራር በግብርና ሚኒስቴር ይወሰናል፡፡

17. **የአፈር ማዳበሪያ አያያዝና ሥርጭት**

የግብርና ሚኒስቴር በወደብ የአፈር ማዳበሪያ አያያዝና አሠራርን በተመለከተ፣ የአፈር ማዳበሪያ አቅራቢዎች፣የአፈር ማዳበሪያ አስመጪዎች እና አስተላላፊዎችን ተግባርና ኃላፊነትን ያካተተ እንዲሁም የአፈር ማዳበሪያ የሥርጭት አውታርን በማስፋት ውጤታማና ቀልጣፋ የሥርጭት ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል መመሪያ ያወጣል፡፡

18. **የተሻረ መመሪያ**

የካቲት 1998 ዓ.ም የወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የአፈር ማዳበሪያ ግዥ፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባትና ሥርጭት አጠቃላይ መመሪያ ተሽሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል፡፡

19. **መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል፡፡

20. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በፌደራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፫/፪ሺ፲፪ መሰረት በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በፍትህ ሚኒስቴር እና በገንዘብ ሚኒስቴር ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ቀን ጥቅምት 05/ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አህመድ ሽዴ